# የጅማ ከተማ ባሕልና ቱሪዝም ጽ/ቤት

## ጅማ የፍቅር ከተማ

ጅማ ካሉት ከኢትዮጵያ እድሜ ጠገብ ከተሞች ውስጥ አንዷና ዋነኛ ከተማ ስትሆን ከተማይቷም በ1822 እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በቀዳማዊ አባጅፋር አባመጋል (አባለንአ) የተመሠረተች ከተማ ነች፡፡ ከተማይቷም ከመዲናዋ አዲስ አበባ በስተደቡብ ምዕራብ በ352 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡

ጅማ በአንጻራዊ መገኛ $7^{0}4'$ እስከ $8^{0}8'$ ሰሜን ላቲትዩድ እንዲሁም $36^{0}14'$ እስከ $37^{0}36'$ ምሥራቅ ሎንግቲዩድ ላይ ትገኛለች፡፡ ከተማዋም በዚህ አንፃራዊ መገኛ ምክንያት በደቡብ ምዕራብ፣ ከሠቃ ጨቆርሳ ወረዳ ጋር፣ ሰሜንና ሰሜን-ምሥራቅ ከማና ወረዳ እና በምሥራቅ ከቀርሣ ወረዳ ጋር ትዋሰናለች፡፡ ጅማ ከባሕር ጠለል በላይ 1725 ሜትር - 1789 ሜትር ከፍታ ላይ ስትገኝ 1789 ሜ. የሚሆነው ከፍታ የሚገኘው ጅሬን የአባጅፋር ቤተመንግስት ያረፈበት ሥፍራ ሲሆን ዝቅተኛ የመሬት አቀማመጥም ማለትም 1725 ሜትር የሚሆነው የሚገኘው በጅማ ትልቁ እስታዲየም ላይ ነው፡፡ የቆዳ ስፋትዋም 100.2 እስኩዌር ኪ.ሜ. ነው፡፡ ይህም ሲታይ ከተማይቷም ካሉት አጎራባች ከተሞች ሰፊና ትልቅ ያደርጋታል፡፡

ጅማ ካሉት የኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ ታሪካዊ እንደመሆንዋ መጠን በውስጧ የተለያዩ ባህላዊ እና ታሪካዊ የሆኑ ቅርሶች ባለቤትም ናት፡፡

1. <u>የንጉሡ አባጅፋር ሁለተኛ ቤተ-መንግሥት፡-</u> ይህ ቤተ-መንግስት ከከተማይቷ 7 ኪ.ሜ. በ1789 ጫማ ከፍታ ላይ ጅሬን በሚባል ሥፍራ ላይ የተገነባ ድንቅና ግዙፉ ታሪካዊ ቤተ-መንግስት ሲሆን ይህም ቤተ-በንግስት በ1870 ዓ.ም. በንጉሥ አባጅፋር ሁለተኛ ዘመን የታነፀ ነው፡፡ ቤተ-መንግስቱም ቲከም በሚባል ሕንዳዊ አማካኝነት ዲዛይን የተደረገ ሲሆን ቤተ-መንግስቱን ለመስራት እንደ ሲሚንቶ ለማያያዣነት ስንዴ፣ እንቁላል እና የኖራ አፈር እንደዚሁም አገር በቀል በሆኑ እንጨቶች ዋንዛ፣ ቀረሮ፣ የአበሻ ጥድ እና ጥቁር እንጨት እንደዚሁም የካቡ ድንጋይ ከ 5 ኪሎ ሜትር የሚሆን ጅሬን አካባቢ በማስመጣት 3000 የሚሆኑ የጅማ አካባቢ በሆኑ የኦሮሞ ጎሳዎች አማካይነት የተገነባ ነው፡፡ ቤተመንግስቱም በውስጡ 29 ክፍሎች፣ 54 መስኮቶችና 65 በሮች ያለው ሲሆን ከ29 ክፍሎች ውስጥ ቤተ-መንግስቱ በውስጡ የቤተሰብ መስኪድ፣ የእንግዳ መቀበያ፣ መመገቢያ አዳራሽ፣ የችሎት ቤት፣ የጥበቃ ክፍል (ማማ) የቤተሰብ መኝታ ክፍል፣ ኃይማኖታዊ ትምህርት መማርያ (መድረሣ)፣ የዕደጥበብ ውጤቶች ማምረቻ ወይም ጅማ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ትታወቅበትን የነበረውን የባህላዊ ውጤቶች ለምሣሌ፡- የእንጨት፣ የቆዳ፣ የሸክላ፣ የብረታብረት፣ የአልባሳት፣ የሀር ምርት የሚሠራበትና፣ የባህላዊ መዝናኛ የሆነውን የትግል ቦታ (ሬስሊንግ) በዉስጡ የያዘ ነው፡፡ በአጠቃላይ ቤተ-መንግስቱን ለመገንባት የወጣው ወጪ ሲሰላ 65 ሺህ ማርትሬዛና 400 ኪሎ ግራም ወርቅ ፈጅቷል፡፡



የአባጅፋር ሁለተኛ ቤተ-መንግስት

2. መስኪድ አፉርተማ እና መካነ መቃብሩ፡-መስኪድ አፉርተማ ከስያሜው ስንነሳ፣ ይህ መስኪድ አፉርተማ የተባለው አበጅፋር ሁለተኛ የተለያዩ የእምነቱ አስተማሪዎች (ዑለማዎችን) ከተለያዩ አካባቢ ማለትም ከሀረር፣ ከወሎ፣ ከአርሲ ከመሣሠሉት ሀገራት አስመጥተው እውቀትን (ኢልም) እንዲያስተምሩ ስለ አስቀመጧቸው ነው ይህ መስኪድ አፉርተማ የተባለው መስኪድም የተገነባው በ1858 አካባቢ በአባጅፋር ሁለተኛ አያት በሆኑት በአባቦቃ አባመጋል ወይም (መሀዲ) በሚባሉት በጅማ ታሪክ በሥድስተኛው ንጉስ አማካኝነት ሲሆን መስኪድም ከተሠሩ በአጠቃላይ እንደ ታሪክ ቀደምትና ጥንታዊ ነው፡፡ ከዚህ መስኪድ ፊት ለፊትም ታሪካዊ የሆነ መካነ መቃብር ያለው ሲሆን በዚህ ታሪካዊ መካነ መቃብር ሥፍራ የታላቁ ንጉሥ አባጅፋር ሁለተኛ፣ የአባታቸው የአባጎሞል አባቦቃ፣ የአያታቸው፣ የባለቤታቸው እንደዚሁም የልጃቸውና የልጅ ልጃቸው መካነ መቃብር በዚህ ታሪካዊ ስፍራ ላይ ይገኛል፡፡

3. ቁባ አባርብ፡-ቁባ አባርብየሚባለው ታሪካዊ የሆነ የቱሪስት መስህብ ሲሆን ከአባጅፋር ቤተ-መንግስት 2 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ጅሬን በሚባል ስፍራ ላይ  የሚገኝ ሲሆን ይህም ታሪካዊ ስፍራ ጅማ ውስጥ ከነበሩ ቀደምት የእምነቱ ሊቅ (ዑለማ) በሆኑት "አባሬብ" አማካኝነት በዘመኑ የተለያዩ እምነታዊ አስተምሮዎችና እምነታዊ ክንዋኔዎች የሚካሄዱበት ስፍራ ነው፡፡ በአሁኑ ሰአት ይህ ታሪካዊ ስፍራ ኃይማኖታዊ ጉብኝት (Religious Tour) ጋር በተያያዘ ሰዎች ከሌላ አካባቢ በመምጣት በአብዛኛው መንፈሳዊ የሆነውን ጉብኝት በማድረግ ላይ ይገኛሉ::




የቁባ አባ አረቡ መስ□ድ

ጅማ ሙዚየም፡- ጅማ ሙዚየም ካሉት የቱሪስት መዳረሻዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ሲሆን ይህም እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር በ1972 ዓ/ም የተመሠረተ ሲሆን ሙዚየሙም የሚገኘው በከተማይቷ መሀል እምብርት በሆነው ፈረንጅ አራዳ ላይ ነው፡፡ በዚህ ሙዚየም ውስጥ የጅማን ስልጣኔ ማለትም ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ከታላቁ ንጉስ አባጅፋር ሁለተኛ እስከ ደርግ ዘመነ መንግስት ያለውን የተለያዩ የጅማ ህዝብ አኗኗር ባህል፣ ታሪክን የሚገልጹ እድሜ ጠገብ የሆኑ ከ1500 በላይ ቅርሶችን በውስጡ የያዘ ሲሆን ይህም ሙዚየም በአጠቃላይ

**ሰባት አበይት** ክፍሎች አሉት እነርሱም፡- ① የታሪካዊ ቅርሶች ክፍል ② ታሪካዊና ባህላዊ አልባሳት ክፍል ③ የማህበረሰብ ማልገያ (Ethnography) ክፍል ④የብሔር ብሔረሰቦች ክፍል

**⑤ ፎቶጋለሪና አርካይቭ ክፍል ⑥ የእንግዳ መቀበያና ⑦የተፈጥሮ ወይም የቅሪተአካል ክፍል በመባል የሚታወቅ ሲሆን ሙዚየሙም ካሉት ሙዚየሞች ውስጥ በቅርስ ብዛት እና በአደረጃጀት የተሸለ ደረጃ ላይ ያለ ሙዚየም ነው፡፡**





**ጅማ ሙዚየም**

**5. ፈረንጅ አራዳ፡- ጣልያን የአድዋን ጦርነት ለመበቀል በኢትዮጵያ ላይ ዳግም በ1928 ወረራ በአካሄደበት ሰዓት መቀመጫ ካደረጋቸው ከተማዎች ውስጥ አንዱ ጅማ ስትሆን ጣልያኖችም ለመጀመሪያ ጊዜ የጅማ ማስተር ፕላንን በ1937 እንደ ኤውሮፓውያኖች አቆጣጠር በእኛ በ1929 ዓ/ም አዘጋጅተዋል፡፡ በዚህም መሠረት አብዛኛውን መሰረተ ልማት የሰሩት ጣልያኖች ሲሆኑ በአብዛኛው የሚገኘው ፈረንጅ አራዳ ላይ ነው፡፡ ፈረንጅ ራዳ ማለት ፈረንጆቹ የሚኖሩበት ሥፍራ ማለት ሲሆን በወቅቱ 5000 ጣልያኖች 2000 አካባቢ አርመኖች፣ ግሪኮች፣ ፈረንሳዮች እና ህንዶች ይኖሩበት የነበረ ሥፍራ ነው፡፡ ጣልያኖቹም ይህንን በመመልከት "ፒኮሎ ሮማ" የሚለውን ስያሜ ሰጥተዋታል፡፡ ትርጉሙም ፒኮሎ ማለት ትንሿ ሲሆን ሮማ ማለትም ሮም ማለት ነው፡፡ ይህንንም ትርጓሜ የሰጡበት ምክንያት ፈረንጅ አራዳ ሮም ካለው ትንሿ ከተማ ጋር ስለምትመሳሰል ነው፡፡ በአጠቃላይ ፈረንጅ አራዳ በጣልያኖች የተዘጋጀ ኪነ ህንፃዎች ያረፈባት ሥፍራ ስትሆን በውስጧም የተለያዩ ሲኒማ ቤቶች፤ ለምሳሌ ሲኒማ ሮማ፣ ሲኒማ ኢታሊያ፣ ሱፐር ማርኬቶች የተለያዩ ሆቴሎች፣ ራስቶራንቶች፣ ማዘጋጃ ቤት፣ የተለያዩ የለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ ለምሳሌ ሊሞናራ እና አረንቻታ፣ የተለያዩ ማከፋፈያዎች ለምሳሌ አቡጀዲቢ ጨርቅ፣ ብርድ ልብስ፣ የአሜሪካን ካኪ ጨርቅ፣ የተለያዩ ጂንሶች፣ ባለሁለት እግር ሳይክል፣ የትምህርት ቤት፣ እርሳስና እስኪሪብቶ፣ ሰንደል፣ ቆዳ ጫማና ሸራ ጫማ፣ ሻማ ጨርቅ የመሳሰሉት በወቅቱ የሚሸጥበት እና የሚከፋፈልበት ሥፍራ ነበር፡፡**

**በአጠቃላይ ፈረንጅ አራዳ የጣልያኖች አሻራ ያረፈበት ሥፍራ ሲሆን በአሁኑ ሰአት የተለያዩ የሀገር ውስጥ ነዋሪዎች ለስራና ለመኖርያ ብሎም ለውጭ ሀገር ዜጎች የቱሪስት መስህብ በመሆን ታገለግላለች፡፡**



ፈረንጅ አራዳ (ፒኮሎሮማ)




ሴንተር ሬድዮ

<u>6. ሴንተር ሬድዮን(Center of Radio)፡-</u> ይህ ታሪካዊ ስፍራ ከጅማ ከተማ 5 ኪ.ሜ. ወጣ ብሎ የሚገኝ ታሪካዊ ሥፍራ ሲሆን ይህም ታሪካዊ የሬደዮ ስቴሽንም የተቋቋመው ከ82 አመት በፊት ልክ ጣልያን እትዮጵያን ዳግም ወረራ ባካሄደበት ወቅት ነው፡፡ ጣልያን በምስራቅ አፍሪካ ካቋቋማቸው ስቴሽኖች ቀደምት ሲሆን ይህም እስቴሽን የተለያዩ ፕሮገራሞችና አዋጆችን በተለያዩ ቋንቋዎች ሲያስተላልፍ ነበር፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡- ①አገር በቀል በሆነው በኦሮምኛ ② በአረብኛ ③ በጣልያንኛ ቋንቋ ነበር፡፡ በአጠቃላይ በአሁኑ ሰአት ይህ ሬድዮ እስቴሽን ማሽኑ በእንግሊዞች አማካይነት በወቅቱ ጣልያኖች ሀገራችንን ለቀው በወጡ ሰአት ከቦታው ተነቅሎ ሱዳን ሀገር የተወሰደ ሲሆን ይህም ማስተላለፊያ በወቅቱ የእምዱሩማን ሬድዮ ጣቢያ በመሆን በሀገረ ሱዳን በማገልገል ላይ ይገኝ ነበር፡፡ ዛሬ ጅማ ላይ ያለው የሬድዮ ማስተላለፊያው በእጃችን ባይኖርም ቀድሞ የነበረው ማሽኑ ያረፈበት ስፍራ እና የማሰተላለፊያ ህንፃው ለሀገሬው ህዝብ ብሎም ለውጭ ሀገር ዜጎች የቱሪስት መስህብ በመሆን እያገለገለ ይገኛል፡፡

<u>7. የቦዬ ሀይቅ፡-</u> ተፈጥሮ ካደለቻቸው ጅማ ውስጥ አሉ ከሚባሉ የቱሪስት መዳረሻዎች አንዱና ዋነኛው ሲሆን ይህም የቱሪስት መስህብ ከከተማው ወደ 6.5 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም የቱሪስት ስፍራ በአብዛኛው የተለያዩ እስከ 108 የሚደርሱ ዝርያ ያላቸው አእዋፋት ከ108 ዝርያዎች ውስጥ 52 የሚሆኑት ወቅታዊ (Seasonal) የተቀሩት ደግሞ አኳቲክ (የሀይቁ) ጥገኛ በመሆን የሚኖሩ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ሰኙን ቢል፣ ሀመርኮፒ፣ ኢጂፕሺያን ፓሮት የመሳሰሰሉትን የምናገኝ ሲሆን በተጨማሪም ጉማሬና ድኩላ በሀይቁ ውስጥና በአካባቢው በሚገኘው ደን ውስጥ ይገኛሉ፡፡



ጅማ ቦዬ ኃይቅ

አዘጋጅ፡ ነጂብ ራያ








GIMMA - IL CINEMA-TEATRO DEL DOPOLAVORO.